## *ወያነ ማን ነው? የትግራይ ህዝብ ወይስ ህወሓት?*

=======================================

*ለውድ የዓይጋ ፎሮም አዘጋጆች በሙሉ ሰላምታየ ይድረሳችሁ፡፡ ሰላም ጤና ይስጥልኝ እንደምን ኣላችሁ፣ የዛሬ ሁለት ወር ገደማ ለመጀመሪያ ጊዜ ኣንድ ፅሁፍ ይዤ ብቅ ብየ ነበር፡፡ ፅሁፌን ለኣንባብያን ስላደረሳችሁልኝም እጅግ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ለዚህም ምስጋናየ የበዛ ነው፡፡ በመሆኑም ይህች ፅሁፌ ለሁለተኛ ጊዜ ላቀብላችሁ ወድጃላሁ፣ ፈቃዳችሁ ከሆነ ወደ ኣንባብያን በማድረስ የተለመደው ትብብራችሁ እጠይቃለሁ፡፡ ኣንባብያንም ይህ የእኔ እና የእኔ ሓሳብ ብቻ መሆኑን በመረዳት እኔን ሳይሆን ሓሳቤን በመንቀፍም ሆነ በመደገፍ ኣስተያየት ብትፅፉልኝ በፀጋ በመቀበል የሚሻሻለውን ለማሻሻል፣ መልስ ለሚያስፈለገውም መልስ ለመስጠት ዝግጁ መሆኔን ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡*

*ወያነ ማን ነው? የትግራይ ህዝብ ወይስ ህወሓት?*

ኣንዳንድ ወገኖች በማወቅ ይሁን ባለማወቅ ነገሮች ሲቀላቅሉ ይታያሉ፡፡ ኣንዳንዶቹ ደግሞ ወያነ ማን እና ምን ማለት መሆኑ ጠንቅቆ ስለሚያውቁ ኣስረግጦ ይናገራሉ፣ ይፅፋሉ፡፡ ላላወቃችሁ እና ነገር ለተቀላቀለባችሁ ወገኖች በሙሉ ወያነ ህወሓትን ፈጠረ ወይስ ህወሓት ወያነን ፈጠረ? የትግራይ ህዝብስ ማንን ፈጠረ? የሚሉ ጥያቄዎች በደንብ በማስተዋል መመርመር ይጠበቅባቿል፡፡ እኔ በተቻለ ኣቅም በገባኝ ልክ፣ በማውቀው እና በሚመስለኝ ለመግለፅ እሞክራለሁ መከታተል ትችላላችሁ፡፡ እኔ እጀምሯለሁ የታሪክ እና የፖለቲካ ሊህይቃን ይጨርሱታል፣ ያብራሩታል፣ ይተነትኑታል፣ ይህ እምነቴ ነው፡፡ የእኔ ስራ ሃሳቡን ማንሳት ብቻ ነው፡፡

ወያነ ማለት ትርጉሙ ለነፃነት መታገል ማለት ነው፡፡ ኣንድ ሰው እከሌ/ሊት "ወየነ" ብሎ ከተናገረ/ች ነፃነት ለማምጣት ለትግል ወጣ ማለቱ/ቷ ነው፡፡ የጭቆና ቀንበር ለመስበር መታገል፣ መስዋእትነት መክፈል፣ ኣልገዛም ማለት ነው፡፡ በትግርኛ "ወያናይ" ማለት ለነፃነት ቆርጦ የተነሳ ታጋይ ወይም በትግርኛ "ተቓላሳይ" ማለት ነው፡፡ያው ወደ እንግሊዘኛው ስንወስደው ሪቮልሽነሪ እንደ ማለት ነው መሰለኝ፡፡ ወደ ጥያቄው መልስ ከመሄዳችን በፊት መጀመሪያ የወያነ እና የህወሓት እድሜ ማየት ግድ ይለናል፣ ከዛ የትግራይ ህዝብ ታሪክ እና እድሜ፡፡ የህወሓት እድሜ ከ1967 ዓ/ም እስከ ዛሬዋ ዕለት ሲቆጠር 43 ዓመታት ገደማ መሆኑ ነው፡፡ የመጀመሪያ ወያነ ትግራይ "ቀዳማይ ወያነ ትግራይ" ስንመለከት ደግሞ ከ1950ዎቹ ኣከባቢ ይጀምራል፡፡ ይህም ወደ 60 ዓመታት እንደሚጠጋ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ወያነ ህወሓትን ፈጠረ እንጂ ህወሓት ወያነን ኣልፈጠረም ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የወያነ እና የህወሓት ውልደት ሲነፃፀር ወያነ የህወሓት ኣባት/እናት የመሆን ዕድሜ ኣለውና ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትግራይ ህዝብ ኣሁን ባለበት ምድር ከ3500 ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ ህዝብ እንደመሆኑ መጠን የመጀመሪያ ወያነ ትግራይ "ቀዳማይ ወያነ ትግራይ"ን ፈጠረ እንላለን እንጂ የመጀመሪያ ወያነ ትግራይ "ቀዳማይ ወያነ ትግራይ" የትግራይ ህዝብን ፈጠረ ኣንልም ( ይቅርታ ከኣማርኛ ኣጠቃቀም የቃላት ኣገላለፅ ከተሳሳትኩኝ ኣርሙኝ)፡፡ የ3500 ዓመታት ዕድሜ እና የ60 ዓመታት ዕድሜ ለንፅፅርም ኣይመጥንም፡፡ ይህ ያልኩበት

ምክንያት ይህ ወያነ የሚል ቃል መሰረቱ ትግራይ ውስጥ ስለሆነ ከትግራይ ህዝብ የበቀለ ነው ከሚል እውነታ ነው፡፡ በመሆኑም ወያነ የህወሓት ኣባት/እናት እንደሆነ ሁሉ የትግራይ ህዝብ ደግሞ የወያነ መገኛ ኣባት/እናት መሆኑ ፈፅሞ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ ወያነ ማለት ነፃነት፣ መገዛት የማይወድ፣ የጭቆና ቀንበር ኣምርሮ የሚጠላ ማለት ከሆነ ይህ የመጣ ከጥንት ኣባቶች ውርስ ነው ማለት ነው፡፡ ኣክሱማውያን ተጋሩ/ኣግኣዚያን (ይቅርታ ይህ ኣገላለፅ ኣሁን በማሕባራዊ ሚድያ ለሚደረግ "ኣግኣዝያን" የሚል እንቅስቃሴ ለመግለፅ ኣይደለም፣ የያኔው "ኣግኣዝያንን" ነው።) ከሚባሉ የተወራረሰ የደም፣ የትውልድ ውርስ ነው፡፡ ያው ኣግኣዚያን ማለት ነፃ ኣወጣ፣ መገዛት የማይወድ፣ ለነፃነቱ የሚሞት እና መስዋእት የሚከፍል ህዝብ ማለት መሆኑ የትግራይ ህዝብ ይቅርና ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብም የሚያውቀው የትግራይ ህዝብ ወርቃማ የስራ ውጤት ታሪክ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በእውነተኛ ስራ የተፈተነ እውነተኛ ተግባር እንጂ የነበር/ተባለ ከሚል ኣፈ-ታሪክ የመጣ ኣይደለም፡፡ ኣሁንም ቢሆን ወያነ በተግባር የሚታይ እና እስከ ዘመነ ምፅኣት ማንም ሰብኣዊ ፍጡር እየመሰከረው የሚኖር ስራ የሚሰራ እንጂ ኣንዳንድ ከሃዲያን እንደሚከዱት እንዳልነበረ የሚጠፋ ስራ ኣይደለም የሚሰራው፡፡ ምክንያቱም ቀደምት የትግራይ ኣባቶች/እናቶች የሰሩት የሀው(የኸው) እስከ ዛሬ ብቻ ኣይደለም እስከ ቀጣይ ትውልድም ህያው ሆኖ እየኖረ ነው፣ ይኖራልም፡፡ የዛሬው ወያነም የትናንትናው ኣግኣዚያዊ ልጅ እንደመሆኑ መጠን ስራው ሁሉ እንደ ኣባት/እናቱ ምንም ሳያዛንፍ የመስራት እና የመከወን ሓላፊነትም ግዴታም ስላለበት በዛው ልክ መስራቱ ይቀጥላል፡፡ ይህ ታሪክ የህዝብ ታሪክ እንጂ የድርጅት ታሪክ ኣይደለም ሊሆንም ኣይችልም፡፡ ህወሓት ከወያነ እንደተወለደ ሁሉ ወያነም የተወለደው ከህዝብ ነው፡፡ የዘመኑ የተጋሩ ቋንቋ ትግርኛ፣ የግእዝ ልጅ ነው፣ የዘመኑ ተጋሩ የቀደምት ኣክሱማውያን ልጆች ነን፣ ወያነም የቀደምት ኣግኣዚ ልጅ ነው፡፡ ምክንያቱም ኣግኣዚ ህዝቡን ነፃ በማውጣት ማንም ዓለም ያልሰራው በዘላለማዊ ታሪክነቱ ወደር ያልተገኘለት የኣክሱማውያን የዓለም ስልጣኔ ጫፍ የደረሰ ስራ የሰራ ሲሆን ወያነም ከ3000 ዓመታት በፊት በኣባት/እናቱ ተጀምሮ ከግቡ ያልደረሰ ወይም ከጫፍ የዓለም ስልጣኔ ቁልቁል የተመለሰ ታሪክ ወደ ነበረበት የከፍታ ማማ ለማድረስ ነው ያለእረፍት ደፋ ቀና እያለ ያለው፡፡ የፖለቲካ ድርጅት ሃገርን በመገንባት የራሱ ድርሻ ያለው ቢሆንም ወሳኙ እና የኣንበሳው ድረሻ የሚወስደው ግን ህዝብ ነው የሚል ፅኑ እምነት ኣለኝ፡፡ ወያነ እና የትግራይ ህዝብ የተለያዩ ናቸው የሚሉ እንደመኖራቸው ሁሉ ሁሉቱም የኣንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው የሚሉም ኣልጠፉም፡፡ ለእኔ <u>ወያነ እና የትግራይ ህዝብ የተለያዩ ናቸው</u> የሚል "እቲ ሓደ ብገርሁ እቲ ሓደ ብጉርሑ" የሚል የትግርኛ ምሳሌያዊ ንግግር ያስታውሰኛል፡፡ ይቅርታ ወደ ኣማርኛ እንዳልተረጉመው ትክክለኛ ትርጉሙ ስለማፃፈ እርግጠኛ መሆን ስላልቻልኩ ነው፡፡ ኣንዳንድ የዋህ ተጋሩ ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ኣይደለም ስለዚህ ወያነ ከህዝብ እያምታታችሁ የህዝብ ስም ኣታጥፉ ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ እነኚህን ነው "እቲ ሓደ ብገርሁ….." ያልኳቸው፡፡ ኣንዳንዱ ደግሞ ውስጣቸው ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት መሆኑን ኣሳምሮ እያወቁ እና እያመኑ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግኘት ብቻ ወያነ እና የትግራይ ህዝብ ኣንድ ኣይደሉም

በማለት ሲሸነግሉን ይሰማሉ (ህወሓት እና የትግራይ ህዝብ ኣላልኩም)፡፡ እነኚህ ደግሞ “........እቲ ሓደ ብጉርሑ”ናቸው፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ቁምነገር ህወሓት ከትግራይ ህዝብ ኣብራክ የወጣች ፖለቲካዊ ድርጅት መሆንዋ ኣይካድም፡፡ ቢሆንም ግን ልጅ እንጂ እንደ ወያነ ራሱ የትግራይ ህዝብ ወይም ኣባት መሆን ኣትችልም፡፡ ወያነ ድርጅት ኣይደለም ህዝብ ነው፡፡ ድርጅትም ሊሆን ኣይችልም፡፡ ድርጅት ሊከስም ይችላል ወያነነት/ትግራዋይነት ግን ዘላለማዊ ነው፣ የተፈጥሮ ሂደቱ ተከትሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተዋረደ/እየተዋለደ እስከ ዘመነ ምፅኣት ይቀጥላል፡፡ ምክንያቱም በእኔ እምነት ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ስለሆነ ነው፡፡ ይህ ለኣንዳንድ የህወሓት ኣባላት እና ደጋፊዎች ሊያስደስታቸውም ሊያሳዝናቸውም ይችላል፣ ለሌሎች ተቃዋሚ ሓይሎችም እንደዛው፡፡ እውነቱ ግን ይህ ነው፣ ምንም ማድረግ ኣይቻልም፣ ተፈጥሮ መቀየር የሚቻልበት ዕድል ጠባብ ነው፡፡ በቃ ወያነነት/ኣጋኣዛውነት የትግራይ ህዝብ የተፈጥሮም የታሪክም መገለጫ ነው፡፡ ከኣጋኣዛውነት የተወረሰ ወያነነት/ትግራዋይነት ነው፡፡ ሌላ ውርስ የለም፡፡ በጥላቻም ሆነ በፍቅር ዓይን ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ነው የሚሉ ወገኖች ልክ ናቸው፡፡ ሰዎች! ተወደደም ተጠላም ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት ነው፡፡ የዛሬ ወያነ ማለት እንደ ቀደምት የተጋሩ ማንነት መገለጫ የሆነው ኣግኣዚ ትዩዩ ስም ነው፡፡ ከፍም ዝቅም ኣይልም፣ እኩል ነው፡፡ የሁለቱም  ቃላት ትርጉም ነፃ ህዝብ መሆን፣ መገዛትን ኣመርሮ መጥላት፣ በኣንድነት በፈረጠመ ጡንቻ ጠላትን ድባቅ መምታት፣ ሁሉ ጊዜ ድልን ማስመዝገብ፣ ኣንፀባራቂ እና ዘመን የማይሽረው ታሪክ መስራት የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ወያነነት/ኣግኣዛዊነት ለኣንድ ፖለቲካዊ ድርጅት የሚሰጥ የቅጥያ ስም ሳይሆን የትግራይ ህዝብ ተቀዳሚ የማንነት መገለጫ ስም ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ወያነነቱ/ኣግኣዛዊነቱ ኣሳምሮ ያውቃል፣ ወያነ ቢሉት ይኮራበታል እንጂ ኣያፍርበትም፡፡ ደግሞ ደጋግሞ ወያነ ቢሉት ስሙ በዓለም ደረጃ ጎልቶ ይወጣል እንጂ ኣይጠፋም፣ ይጎመራል እንጂ ኣይሳሳም፣ በንፁ ወርቅ የተፃፈ ታሪኩ ይደምቃል እንጂ ኣይጠለሽም፡፡ ምክንያቱ የህዝቡ እውነተኛ ስሙ ወያናይ/ትግራዋይ ስለሆነ ነው፡፡ ወዳጅም ይሁን ምቀኛ በጥሩም ሆነ በክፉ የወያነ ስም ሺ ጊዜ ያነሳሉ እስከ ዘላለምም እያነሱ ይኖራሉ፡፡ ይህ ለእኛ ደስ ይለናል፡፡ እኛ በቃ ወያነ/ኣግኣዚያን ነን፡፡ ነፃ ኣውጪ ነን፣ መገዛት ኣንወድም፣ ለወዳጅ ፍቅርን ኣብዝተን እንለግሳለን፣ ለጠላት መጀመሪያ ምክር እምቢ በማለት እኛን ለመጉዳት ለሚመጣ ደግሞ ያው የታወቀ ነው ልኩን እስከሚያውቅ የእጁን ኣግኝቶ ላይመለስ እስኪፈረጥጥ መቅጣት ነው፡፡ በቃ ወያናይ/ትግራዋይ ማለት ይህ ነው፡፡ ወያነ/የትግራይ ህዝብ ሲበዛ ታጋሽ፣ ኣስተዋይ እና ሰው ኣክባሪ ፍጥረት ነው፡፡ በዘፈቀደ በስሚ ስሚ ተነሳስቶ ማንንም ለመጉዳት ኣይቸኩልም፡፡ በብዙ ትዕግስት ብዙ ፈተና ያልፋል፣ ያሳልፋል፡፡ “የተኛ ኣንበሳ የሞተ ይመስላል” እንዲሉ ወያነ/የትግራይ ህዝብ የሚደርስበት ግፍ እያየ እንዳላየ፣ እየሰማ እንዳልሰማ በሆደ ሰፊነት ነገሮችን በከፍተኛ ትግስት ያሳልፋል ልክ ኣሁን እየተፈፀመበት እንዳለ ግፍ ማለት ነው፡፡ ጦር መማዘዝ የከፋ ጉዳት እንጂ ቅንጣት ታክል ጥቅም እንደሌለው ከወያነ/የትግራይ ህዝብ በላይ የሚረዳ ማንም ፍጡር

የለም፡፡ ለዛም ነው ሰዎች ሲነሱበት ተሎ ከመነሳት በመቆጠብ በሰከነ ኣእምሮ ተረጋግቶ ነገሮችን ለመመርመር፣ ለመረዳት እና ለማሰብ ጊዜ የሚወስደው፣ ለችኩሎችም ደግሞ ደጋግሞ እንዲያስቡ ጊዜና ዕድል የሚሰጣቸው፡፡

ወያነ/የትግራይ ህዝብ ኣንድ እና ፈፅሞ ልዩነት እንደሌላቸው ውስጣቸው እያወቀ ድንገት ምኞታቸው ሰምሮ ተለያይቶ ማየት ሲመኙ ከነበሩ እጅግ በጣም ብዙ ቡዱኖች ዛሬ ላይ ተስፋቸው ተሟጦ በውስጣቸው ለዘመናት እያዳበሩት የነበረ ሃቅ ኣሸንፎ ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት መሆኑን ግልፅ በማድረግ ወያነ/ትግሬ ከምድረ-ገፅ እናጥፋው የሚል የዘር ማጥፋት ኣዋጅ በማስነገር በትግራይ ህዝብ የዘር ማጥፋት ውጥን ወጥነው መጥቷል፡፡ ከነዚህ ኣንዱና ግንባር ቀደሙ "ቤተ-ኣማራ" የሚባል የደርግ ልቅምቃሚ ተሰባስቦ ያኔ በወያነ ኣይበገሬነት በትጥቅ ትግል የደረሰበት ሽንፈት እና ውርዴት ለመበቀል ትግራዋይ ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት ግልፅ የዘር ማጥፋት ኣዋጁን በተደጋጋሚ እያስለፈፈ ይገኛል፡፡ በእኔ እምነት "ቤተ-ኣማራ" የኣማራ ህዝብ ይወክላል የሚል ግምት የለኝም፡፡ ምክንያቱም ወያነ/የትግራይ ህዝብ ለወንድም የኣማራ ህዝብ ልክ እንደራሱ ዕቅፍ ድግፍ ኣድርጎ ከደርግ የቦንብ እና የጥይት እሩምታ ያድናል እንጂ ህዝብን የመጉዳት ባህልም ተግባርም እንደሌለው ዋናው ምስክሩ ራሱ የኣማራ ህዝብ ነው ብየ ስለማምን ጭምር ነው፡፡እንደ እኛ እምነት ደርግና የኣማራ ህዝብ የተለያዩ ናቸው፡፡ ደርግ ከመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተሰበሰበ ሰራዊት የያዘ ነብሰ በላ ኣረመኔ ወተሃደራዊ ስርዓት መሆኑን እንጂ ኣማርኛ ስለተናገረ ብቻ ደርግ ኣማራ ነው ያለ ሰው የለም፡፡ ካለመረዳት የሚቀላቀልበት ሰው ካለም መታረም ኣለበት፡፡ ደርግ ራሱን እንጂ ማንንም ብሄር ኣይወክልም፡፡ ብሄርን ቢወክል እማ የደርግ ፍርፋሪ ለማግኘት ሲሉ የትግራይ ጓዳ ጎድጓዳ የሚያውቁ ከትግራይ ህዝብ የበቀሉ ጥቂት የደርግ ባንዳዎች በመሆን የትግራይን ህዝብ ኣስጨፍጭፈዋል፣ ጨፍጭፈዋልም፡፡ እነዚህ ደርጋውያን እንጂ ትውልደ ትግራይ ስለሆኑ ብቻ የትግራይን ህዝብ በነዚህ ስራ የታሪክ ተወቃሽ መሆን ኣይችልም፡፡ ከኣማራ ህዝብ የወጡ ከህዝቡ ብዛት ኣንፃር ጥቂት ሊባል በሚችል ኣግባብ የደርግ ኣቀንቃኞች እና ለመናገሩ በሚከብድ ብዙ ግፍ የሰሩ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ታድያ እኚህ ግፈኞች የኣማራ ህዝብ የሚወክሉ ናቸው ኣልተባለም፡፡ ደርግ ራሱን ነው የሚወክሉት እንጂ፡፡ ወያነ/የትግራይ ህዝብ በኣማራ ህዝብ ግፍ ሊፈፅም ይቅርና ለደርግ ሰራዊት እንኳን ከማረካቸው በኃላ ኣልብሶ እና ኣስተምሮ ወደ ሃገራቸው እና ቤተሰቦቻቸውን ነው በሰላም የመለሳቸው እንጂ ደርጋውያን እንዳደረጉት በህይወት እያሉ ጉድጓድ ቆፍሮ ኣልቀበረም፡፡ ደርጋውያን ግን የሰራችሁት ግፍ የእነ ጀግና "ተቓላሳይ" ኣሞራ እና ጀግና "ተቓላሲት" ቀሺ ገብሩ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ስለሆነም ደርግ በደርግነቱ እንጂ በኣማራነቱ፣ በኦሮሞነቱ፣ በትግራዋይነቱ የፈረጀ እና ጣት የቀሰረበት ኣካል ያለ ኣልመሰለኝም፡፡ የለም እኛ ደርጋውያን ስለሆንን ደርግን ያባረረ/ያጠፋ ጠላታችን ነው፣ እሱን ሳናጠፋ ኣገር የለንም የሚል ኣቋም ይዞ የሚመጣ ካለ ወያነ/የትግራይ ህዝብ በድጋሚ በደርጋውያን እጅ መግባት እና ሞት ኣንድ ስለሚሆንበት እንደወትረው ኣይቀጤ ቅጣት እንደሚቀጣው ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ በዘለለ ግን ወያነ/የትግራይ ህዝብ በማንም ኢትዮጵያዊ የሰራው ግፍም በደለም የለም፡፡ ይህ ከላይ

በስም የተጠቀሰ “ቤተ- ኣማራ” ነኝ ባይም የኣማራ ህዝብ ወክሎ የመጣ ሳይሆን ትላንት  ለኣማራ ህዝብም ጭምር ሲጨፈልቅ እና ሲገድል የነበረ የደርግ ስብስብ ነው፡፡ ለዚህም ነው ወያኔ/ትግሬ ከምድረ-ገፅ የማጥፋት ተቀዳሚ ዓላማየ ነው የሚለን፡፡ ወያነ/የትግራይ ህዝብ ጨካኙ ስርዓት እንጂ ማንም ህዝብ ለማጥፋትም ኣልተነሳም፣ ኣላጠፋምም፡፡ ቢያጠፋ እያንዳንዱ የደርግ ባለስልጣናት እና ቤተሰዎቻቸው በጠፉ ነበር፣ ትልልቅ ወንጀል የሰሩ ጭምር በምህረት እንደተለቀቁ ይታወቃል፡፡ በኣንድ ቀን በውሱን ሰዓታት ከ2500 ያላነሰ የሓውዜን ህዝብ በገበያ ቀን በግፍ በጦር ኣውሮፕላን የጨፈጨፉ፣ የሰው እና እንስሳት ኣካላት ለመለየት እስከሚከብድ እና ከተማዋ በደም ጎርፍ እንዲጥለቀለቅ የፈረዱ እና የፈፀሙ እንኳን  በይቅርታ ተለቀዋል፡፡ ሆደ ሰፊነት ይህ ነው፡፡ ይቅር ባይነት ይህ ነው፡፡ ይህ ይቅርታ እና ምህረት የሰጠ ወያነ/የትግራይ ህዝብ ነው፡፡ ወያነ/የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ በደል እንደፈፀመ የሚያራግቡ እና ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሳሳተ እና የሚያነሳሳ መረጃ በመስጠት በዚህ ንፁህ ህዝብ ጣታቸውን እንዲቀስሩ የሚሰሩ ደርጋውያን ትላንት ያጥዋትን ስልጣን ከመንግስት በመንጠቅ የተለመደው ነውራም ተግባራቸው በድጋሚ በኢትዮጵያ ህዝብ ለመፈፀም ዕድል ካገኙ ጥረት ማድረጋቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ የትግራይ ህዝብ ይህ የደርጋውያን ለስልጣን ጥድፊያ ምን ለማድረግ እንደሆነ በመረዳት ዛሬም እንደትላንቱ ወያነነቱ መታጠቅ ግድ ይለዋል፡፡ ያው ትግራዋይ ሁሌም በወያነነቱ ባይታማም ከምንም ጊዜ በላይ ወያነነቱ ማጠናከር የሚያስፈልገው ደግሞ ኣሁን ነው፡፡ ኣትሳሳቱ ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ነው!! (ኣሁንም ወያነ እንጂ ህወሓት ኣላልኩም)ምክንያቱም ወያነ ህዝብ ሲሆን ህወሓት ድርጅት ናት፡፡ ወያነ ሙሉውን የትግራይ ህዝብ ማለት ሲሆን ህወሓት ግን ኣንድ ኣራተኛ (1/4) የትግራይ ህዝብ እንኳን ስለመሆኑ እርግጠኛ ኣይደለሁም ነገር ግን ቢያንስ እንጂ ከዚህ በላይ ግን ኣይሆንም፡፡ ለዚህም ነው ህወሓት ማለት የትግራይ ህዝብ ነው ለማለት ያልደፈርኩት፡፡ ነገር ግን፡-

ኣትሳሳቱ **<u>“ወያነ ማለት የትግራይ ህዝብ ነው!!”</u>**

ኣይደለም የሚል ካለ ማጣቀሻዎችን በማቅረብ ሊፅፍልኝ ይችላል፡፡

“ወዲ ጇ ” ነኝ!!

ታህሳስ 21 ቀን 2010 ዓ/ም

ኢትዮጵያ